# የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ግንቦት ቅጽ 1 ቁጥር 12


## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን ግቦች ለማሳካት የኩባንያው ምርት አቅርቦት ክፍል ድርሻ ወሳኝ መሆኑ ተገለጸ።

የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ምርት መጋዘን እና አቅርቦት ክፍል በንግድ ትስስር ውስጥ ያለውን የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት በማስወገድ አምራቹን ማኅበረሰብ በቀጥታ ከሸማቹ ጋር ለማገናኘት ብሎም ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምርቶች በበቂ ሁኔታ በማቅረብ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተገለጸ።

ምስል በ ኤደን ደነቀ




> “
> **10 በመቶ ብቻ በሆነ የእሴት ጭማሪ ግልጽ እና ነጻ የሆነ የግብይት ሥርዓት ዘርግቶ የግብርና እና የማቀነባበሪያ ውጤቶችን ለገበያ የሚያቀርበውና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ብሎም የገበሬውን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በትኩረት የሚሠራው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አምራቹ ልፋቱን የሚመጥን ዋጋ እንዲያገኝ ሸማቹም ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገበያይ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል ሲሉ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የምርት አቅርቦት ክፍል ዋና ኃላፊ ወ/ሮ ፍሬሕይወት ገ/ሕይወት ተናግረዋል።**

ኩባንያው በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነትን ታሪክ የማድረግ ውጥኑ እውን እንዲሆን ሸማቹን ማኅበረሰብ ከአምራቹ ጋር በቀጥታ የማገናኘት ሥራዎችን በኦንላይን ወይም 9858 ላይ ደውሎ በማዘዝ አልያም በቤት ለቤት አገልግሎት ተደራሽ ሲያደርግ መቆየቱን ያወሱት ኃላፊዋ የፐርፐዝብላክ ኢቲኤችን እንቅስቃሴ በተመለከተ እንዲሁም በጋራ በሚከወኑ ሥራዎች ዙሪያ ከምርት አቅራቢዎችና አምራቾች ጋር በመምከር የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ከማዘጋጀት ባሻገር ከበርካታ ድርጅቶች ጋር ውል በመፈጸም ወደ ተግባር መገባት ተችሏል ብለዋል።

ጥራታቸውን የጠበቁ የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶችን እንዲሁም የእንስሳት ተዋጽዖዎችን በየቀኑ ወደ ዋናው መጋዘን እና ሱቆች በማስገባት በቂ የሆነ ምርት መጠን እንዲኖር ብሎም ለሸማቹ እንዲደርስ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች መሠራታቸውንም ወ/ሮ ፍሬሕይወት ጠቁመዋል።

ለኩባንያው ምርት አቅራቢዎች የሚፈጸመውን የገንዘብ ክፍያ በተመለከተም “የእንስሳት እና ፍራፍሬ ምርቶችን ለሚያቀርቡ አምራቾች እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ምርት አቅራቢዎች በገቡት የውል ስምምነት መሠረት የምርት አቅርቦት ክፍሉ ክፍያ እንደሚፈጽም ዋና ኃላፊዋ ገልጸዋል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አሁን ላይ ቀጥታ ከገበሬዎች ከሚያገኘው ምርት በተጨማሪ ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪን ጨምሮ አልሜታ ኢምፔክስ፣ ቬጅ ቦክስ ሆርቲካልቸር እና ኢትዮ ቬጅ ፍሩት ከተሰኙ የእርሻ ምርት አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሥራት ላይ እንደሚገኝና የገበያ ጥናት ከማካሄድ ጀምሮ የአዳዲስ ምርቶችን ዝርዝር እና ዋጋ የማሳወቅ ተግባር በምርት አቅርቦት ክፍሉ እደሚከወን ተገልጿል።

የምርት አቅርቦት ክፍሉ ጥራት ያለው የመረጃ እና የሪፖርት ግንኙነት ሥርዓት በመዘርጋት ከሁሉም የኩባንያው ክፍሎች ጋር በጥምረት ከመሥራቱ በተጨማሪ የምርት አቅራቢዎችን ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ መሆኑን የክፍሉ ዋና ኃላፊ ጠቅሰው በየቀኑ በሚያደርገው የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ መሠረትም ሁል ጊዜ በ3 ቀናት ልዩነት የምርት ዋጋ ማስተካከያ እንደሚያደርግና መረጃውን በአጭር የጽሑፍ መልእክት ለተጠቃሚዎች የማሳወቅ ሥራ በትኩረት ሲከናወን መቆየቱን አስታውሰዋል።

ወቅትን ጠብቀው የሚመረቱ የእርሻ ውጤቶች ምርት እጥረትና መጥፋት፣ የአየር ሁኔታ ለውጥ፣ የመንገድ እና ትራንስፖርት ጉዳዮች እንዲሁም የሃገሪቱ ወቅታዊ የጸጥታ ሁኔታ በምርት አቅርቦቱ ላይ ጫና ማሳደራቸውን የገለጹት ወ/ሮ ፍሬሕይወት ኩባንያው በሚያለማው የራሱ እርሻ አማካኝነት እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ እንደሚቻልና ከእስካሁኑ በተሻለ ዋጋ እና ጥራት ምርቶችን ለተጠቃሚው ለማድረስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ይፋ አድርገዋል።

## የከገበሬው ቴክኖሎጂ ዲጂታል አደፕሽን ግብረ ኀይል የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን እንቅስቃሴ ቀልጣፋ ለማድረግ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል ተባለ።

ምስል በ ኤደን ደነቀ



> “
> **ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የጥቁርን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ የበላይነት የማረጋገጥ ራዕዩን እውን ለማድረግ የሚያስችለውን ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂ ተግባር ላይ ለማዋል የከገበሬው ቴክኖሎጂ ዲጂታል አደፕሽን የተሰኘ ግብረ ኀይል ማቋቋሙን የክፍሉ ኀላፊ እና የቦርዱ ጸሐፊ ወ/ት ሩት ገብሩ አስታወቁ።**

ግብረ ኃይሉ ከሁሉም የኩባንያው የሥራ ክፍሎች በተለይም ከምርቶች ሽያጭ ጋር ግንኙነት ካላቸው ክፍሎች የተውጣጡ ኃላፊዎችን ያካተተ ሲሆን በዋናነት በኩባንያው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ አስፈላጊው የቴክኖሎጂ ሥርዓት እንዲተገበር የማስቻል እና በጋራ ከሚሠሩ የቴክኖሎጂ ተቋማት ጋር ያለውን አጠቃላይ ሒደት የመቆጣጠር ድርሻ ይኖረዋል ተብሏል።

የግብረኃይሉን አጠቃላይ ተግባር በተመለከተም ከዚህ ቀደም በኩባንያው ሥራ አመራር ውሳኔ መሠረት በጥቂት ክፍሎች ከሚከወኑ የቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች በቀር ራሱን ችሎ ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮችን የሚያስተዳድር ክፍል አለመኖሩን በመጠቀም የኩባንያውን ድረ ገጽ ከማበልጸግ ጀምሮ የተለያዩ ጉዳዮችን ለማከናወን የሚያስችሉ መተግበሪያዎችን እና ፈጠራዎችን እስከመሥራት የሚዘልቁ ተግባራትን በትኩረት የሚከታተል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አስፈላጊነቱ አሳማኝ መሆኑን የማርኬቲንግ ክፍል ዋና ኃላፊና የፐርፐዝብላክ ቴክኖሎጂ ዲጂታል አዶፕሽን አባል አቶ ታደለ ሰይፉ አብራርተዋል።

ኃላፊው አክለውም ኮሚቴው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን በሚያሳትፉ የቴክኖሎጂ ርዕሰ ጉዳዮች በመወያየት እና በመፈተሽ የማጽደቅ፣ ከቴክኖሎጂ ነክ ተቋማት ጋር አብሮ የመሥራት ጥያቄዎች ሲቀርቡ ገምግሞ የመወሰንና አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ ኃላፊነቶች እንዳሉበት አውስተው ለአብነትም እንደ ሳንቲም ፔይ፣ ቴሌ ብር እና ቻፓ ካሉ የክፍያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ ስምምነቶችን በተግባር ለማስቀጠል የተለያዩ ሥራዎች መጀመራቸውን አንስተዋል።

ግብረ ኃይሉ ከዚህ በፊት በነበረው አሠራር ከጋራ መግባቢያ ሰነድ መፈራረም በኋላ የሚታዩ የግንኙነት መላላቶችን ለማስወገድ ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል የተባለ ሲሆን የሽያጭ እና ግዢ ክንውኖችን ጨምሮ  የድርጅቱን አጠቃላይ የስራ ሒደት ለመከታተል የሚያስችሉ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ተግባራት በታቀደላቸው መንገድ በጥራት እንዲከናወኑ እና ለክትትል ምቹ ከባቢ እንዲፈጠር እንደሚያደርግ ተገልጿል።

## በከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር ቅርንጫፍ ቢሮዎች ውጤታማ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸው ተገለጸ።

1,000,000 ገበሬዎች አክሲዮን በመግዛት የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ባለቤት በመሆን እንዲሁም በዘመናዊ ግብርና ከኩባንያው ጋር በጥምረት በመሥራት ሕይወታቸውን የሚያሻሽሉበትን ዕድል ለማመቻቸት የተቋቋመው የከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር በመላው ኢትዮጵያ እስካሁን ባከናወናቸው እንቅስቃሴዎች 18,864 ገበሬዎችን ባለአክሲዮን በማድረግ 6,372,145 ብር መሰብሰብ ችሏል ሲሉ የቴክኒካል ኦፕሬሽን ክፍል ዋና ኃላፊ አቶ አስናቀ ኃ/ሚካኤል ገለጹ።

በነሐሴ 2014 ወደሥራ የገባው ፕሮጀክቱ እስከ ሰኔ 2015 ዓ.ም 30 ቅርንጫፎችን ለማደራጀት ዐቅዶ እስካሁን 6 የክልል ማስተባበሪያ እና 11 ቅርንጫፍ ቢሮዎችን መክፈት ችሏል ያሉት ኃላፊው የግብርና  ሜካናይዜሽን አገልግሎቱን የሚመሩ፣ የሚያደራጁ፣ የሚያስተባብሩና የሚቆጣጠሩ ባለሞያዎችን በመቅጠር ዋናውን መሥሪያ ቤት ጨምሮ ከ200 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን አስረድተዋል።

KIEP
KEGEBEREW INTEGRATED EXTENSION PROGRAM

በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብሩን የሚያከናውኑ ሠራተኞችን ለመቅጠር ዋናው መሥሪያ ቤት በየደረጃው ካሉ የግብርና ቢሮዎች ጋር በመሆን የምልመላ እና የቅጥር ተግባራት እንደሚያከናውን የተናገሩት አቶ አስናቀ አስፈላጊነቱን መሠረት አድርጎ የምደባና የድልደላ ሥራዎችም እንደሚሠሩ ይፋ አድርገዋል።

የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር ቅርንጫፍ ቢሮዎችም በዋናነት ገበሬዎችን በክላስተር የማደራጀት፣ ጥራታቸውን የጠበቁ የግብርና ጥሬ እቃዎችን ለገበሬዎች የማቅረብ እንዲሁም የኩባንያውን አክሲዮኖች የመሸጥ ኃላፊነቶችን እንደሚወስዱ የመርሐግብሩ ሥራ አስኪያጅ አቶ አብርሃም ተፈረደኝ ተናግረዋል።

አቶ አብርሃም አክለውም የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር በተለያዩ ከተሞች በከፈታቸው ቅርንጫፍ ቢሮዎች 1,000,000 ገበሬዎች ከፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ባለአክሲዮንነት ባለፈ ከኩባንያው ጋር በአንድነት በማልማት ትርፋማ እንዲሆኑ የሚካሔዱት ተግባራት ውጤታማነት እየተስተዋለ መሆኑን ጠቅሰው በቅርቡ በተደራጁ 4 ክላስተሮች ዘር በመረከብ የእርሻ ሥራ መጀመሩን አስታውቀዋል።

እ.አ.አ በ2026 30 ሺ ሄክታር መሬት የማልማት ውጥን የያዘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር አሁን ላይ በተደራጁት ክላስተሮች ዝግጁ የሆነ 1786 ሔክታር መሬት ወስዶ የማልማት ሒደት ላይ ሲሆን በቀጣይም ክፍሉ የክልል ቅርንጫፍና ማስተባበሪያ ቢሮዎችን ይበልጥ በማቀናጀት ከገበሬው ማይክሮ ፋይናንስ እና ከገበሬው ኢንሹራንስ ኩባንያ የማቋቋም፣ በርካታ የከገበሬው ምርት መሰብሰብያና ማሰራጫ ጣብያዎችን የማደራጀት ውጥን እንዳለው ተገልጿል።

10,000 ክላስተሮችንም በማቋቋም በሀገሪቱ ትልቁን የኩታ ገጠም እርሻ (ክላስተር) አስተዳደር መመስረት ከግቦቹ መካከል ዋነኛው መሆኑ ይፋ ተደርጓል።

## ከገበሬው ኢ ኮሜርስ  ሁሉም የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ደንበኞች ሻጭ እና ገዢ መሆን የሚችሉበትን የከገበሬው መተግበሪያ በይፋ ሊያስጀምር ነው።

ምስል በ ኤደን ደነቀ



“

**ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በከገበሬው ኢ-ኮሜርስ አማካኝነት ደንበኞች የከገበሬው ምርቶች እና አክሲዮን ለመሸጥ የሚያስችላቸውን መተግበሪያዎች በይፋ ሊያስጀምር መሆኑን የከገበሬው ኢኮሜርስ ዳይሬክተር አቶ አማኑኤል መለሰ አስታውቀዋል።**

ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም በተሰኘ የግብይት መድረክ ልዩ ልዩ ምርቶችን ለተጠቃሚዎች ለማከፋፈል እንዲሁም ምርት ለክፍለ ሃገር በሚል ተነሣሽነት ምርቶችን በመላው አገሪቱ ለሚገኙ ደንበኞች ለማቅረብ እየሠራ የሚገኘው የከገበሬው ኢ-ኮሜርስ ሁሉም ሻጭና ገዢዎችን በቀጥታ በማገናኘት የከገበሬው ምርቶች እና የኩባንያውን አክሲዮኖች ለመሸጥና ለመግዛት የሚያስችል መተግበሪያን አበልጽጎ ወደ ሥራ ለማስገባት ቅድመ ዝግጅቶችን ማጠናቀቁን ገልጿል።

መተግበሪያዎቹ ማንኛውም ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ጋር ለመሥራት ፍላጎት ያለው ግለሰብ ከድርጅቱ የመለያ ቁጥር በመውሰድ በኦንላይን ግብይት የከገበሬውን የግብርና እና ማቀነባበሪያ ምርቶች እንዲሁም የኩባንያውን አክሲዮኖች በመሸጥ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሲሆኑ የወኪልነት መለያ ቁጥር ባላቸው ግለሰቦች አማካኝነት ምርት ወይም አክሲዮን የሚገዙ ደንበኞች የወኪሎቹን ቁጥር አስመዝግበው ሲገበያዩ በከፈሉበት ፍጥነት  ወኪሎች ኮሚሽን እንዲያገኙ እንደሚስችላቸው ይፋ ተደርጓል።

የመተግበሪያ ማበልጸግ ሒደቱ 80 በመቶ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቅቋል ያሉት ኃላፊው ኩባንያው ከዚህ ቀደም በነበረው የከገበሬው መተግበሪያ ካካተታቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ የተለያዩ አዳዲስ ገጽታዎች መያዙንም አስታውሰዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ይጠቀምበት የነበረውን የከገበሬው የጥሪ ማእከል ይበልጥ በማዘመን ወደሥራ ሊያስገባ መሆኑን ያስታወቀ ሲሆን ለጥሪ ማእከሉ ግንባታ አስፈላጊው የዝርጋታና የእቃ ግዢ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው ሲሉ አቶ አማኑኤል ገልጸዋል።

ቀደም ሲል የከገበሬው ኢ-ኮሜርስ የአገልግሎት አድማሱን ይበልጥ ለማስፋት ከግብርናና የማቀነባበሪያ ውጤቶች በተጨማሪ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ከአምራቾች ተረክቦ ለሸማቾች የሚያደርስበትን የሎጂስቲክስ ሥርዓት በመዘርጋት ላይ መሆኑን ይፋ ማድረጉን ያስታወሱት ኃላፊው በመላ አገሪቱ ከሚገኙ አምራችና ሸማቾች እንዲሁም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች በ 9858 እንዲሁም በ 7151 የሚደረጉ ጥሪዎችን በማስተናገድ ከፐርፐዝብላክ ጋር ግልጽ እና ጤናማ ትስስርን በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋልም ብለዋል።


**ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ**

**ሲኒየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና**

**ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ**



## ለበለጠ መረጃ

ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com